# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org መስከረም 1997 September 2004

ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።

“ምላሳቸውን ስለ ሐሰት እንደ ቀስት ገተሩ፤በምድር በረቱ ነገር ግን ለእውነት አይደለም፤ከክፋት ወደ ክፋት ይሄዳሉና እኔንም አላወቁምና ÷ ይላል እግዚአብሔር። ወንድምም ሁሉ ያሰናክላልና፥ ባልንጀራም ሁሉ ያማልና እናንተ ሁሉ ከባልንጀሮቻችሁ ተጠንቀቁ፥ በወንድሞቻችሁም አትታመኑ። ሰውም ሁሉ ባልንጀራውን ያታልላል፤በእውነትም አይናገርም፤ ሐሰትን መናገርንም ምላሳቸው ተምሮአል፥ ክፋትን ለማድረግ ይደክማሉ። (ትንቢተ ኤርምያስ 9÷3-5)

“ጥላቻውን የሚሸሽግ ሐሰተኛ አንደበት ያለው ነው፤ሐሜትን የሚዘራ ሁሉ ተላላ ነው።” (መጽሐፈ ምሳሌ 10÷18። አ/መ/ት)

## ሐሜት ነቀፋና ትችት

ሐሜትና ትችት ታላቅ የጥፋት መሣሪያ ናቸው። ሰዎችን ስንተች ወይም ስናማ የሚታማውን ሰው ስም እንጐዳለን። የሰሚውን ሰው አእምሮ ደግሞ እናቆሽሻለን። ሐሜተኛው በማማቱ ÷ ተባባሪውም ፈቅዶ በመስማቱ የታማውም በመታማቱ፥ሁሉም እኩል ከሳሪዎች ናቸው። ሐሜተኞች በእግዚአብሔር ፍርድ፥የታማው ደግሞ በሐሜተኞች ፍርድ የተጎዱ ናቸው። በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ ከመውደቅ ያድነን።

በመዝሙረ ዳዊት 15 ላይ “አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?” በማለት ለቀረበው ጥያቄ ከተሰጡት መልሶች አንዱ፥ በቁጥር 3 የተጠቀሰው፡ “በአንደበቱ የማይሸነግል፥በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ፥ዘመዶቹንም የማይሰድብ።” የሚለው ነው።በእግዚአብሔር ድንኳን (ዘንድ) ክፋትና የአንደበት ሽንገላ ይዘን ልንኖር እንደማንችል የሚያስረዳ ነው።

### ሐሜትንና ተቺነትን ለማስወገድ የሚረዱ ምክሮች ፡-

ማንኛውንም ክፉ ልማድ መላቀቅ ቀላል እንዳልሆነ የታወቀ ነው። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከመምጣታችን በፊት የለመድናቸውን የኃጢአት ባሕሪያት ለመላቀቅ ምን ያህል እንደሚያስቸግር በራሳችን አይተናል። አንዳንዶቹ ባሕሪያት ደግሞ ከዓመታት የክርስትና ሕይወት በኋላ እንኳ ያልተላቀቅናቸው ይኖራሉ። ይህም የሚያሳየው ቅድስና ያለ ብዙ መጋደል እንደማይገኝ ነው።

### ስለቅድስና መፀለይ፡-

የትችትንና የሐሜትን ፈተና ለመቋቋም የሚያስችል ኃይል እንዲሰጥህ ወደ ጌታ ፀልይ። አዘውትረህ ስለ ሌሎች የምታስበውንና የምትሰጠውን አስተያየት አስተውል። ተጠንቀቅም። አስከ ዛሬ ድረስ ስላማሃቸውና ስለ ነቀፍካቸው ሰዎች፥ በጌታ ፊት በመናዘዝ ንስሐ ግባ። እግዚአብሔር እንዳያርምህ እንቅፋት የሆነብህን ትዕቢትንና ፍርሃትን ትተህ ለመንፈስ ቅዱስ ተግሳጽ ልብህን ክፈት።

### ለጎዳናቸው መፀለይ፡-

ሆነ ብለህ በማወቅ ወይም በዘልማድ ባለማስተዋል ክፉ ለተናገርህባቸው ሰዎች ከልብ ፀልይ። ይህ አድራጎት ከምትፀልይላቸው እኩል፥አንተንም ይፈውስሃል። በተመሳሳይ አኳኋን አንተን ለጎዱህ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው ፀልይላቸው። በእግዚአብሔር አሠራር ሰውን አስረው እያሉ መፈታት ስለማይቻል፡- የበደሉህን ይቅር በማለት በጌታ ቅርበት ውስጥ መመላለስ እንዲችሉ ፀልይላቸው

### ራስን መመርመር፡-

ሐሜትንና ነቀፋን ለማስወገድ የሚቸግርህ ለምን እንደ ሆነ ራስህን በመመርመር በምታገኘው ጉድለት አኳያ ፀጋ እንዲበዛልህ ጹምና ፀልይ ። እግዚአብሔር የልብ ንጽሕና እንዲሰጥህ ተግተህ አሳስበው።

### ልብን መጠበቅ፡-

ብዙ ቅዱሳን ከዚህ ክፉ ባሕሪይ እየተላቀቁ ቢሆንም ብዙዎች ደግሞ ሐሜትን የሚራቡና የሚጠሙ በዙሪያህ ስለማይታጡ፥ ነገራቸውን ሊያካፍሉህ እንደሚሞክሩ በማወቅ ተጠንቀቅ። እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥምህ የምትወጣበትን ፀጋ እንዲያበዛልህ ፀልይ።

### ሐሜተኞችን መቋቋም፡-

ሐሜተኞች በፊትህ ሰውን አንስተው ማማትና መንቀፍ ሲጀምሩ የሚከተሉትን የመሰሉ ጥያቄዎች በመጠየቅ ኃላፊነት እንዲሰማቸው መርዳት ትችላለህ፡- ይህንን መስማት ለእኔ ለምን አስፈለገ? ይህንን ወሬ ከማን ሰማኸው? ስለዚህ ነገር የሚመለከታቸውን አነጋግረሃል? ስለዚህ ሰው ፀልየሃል? ይህንን ነገር ከመስማቴ በፊት ለምን እንደምትነግረኝ አስረዳኝ ወዘተ።

### “ሳያረጋግጡ ወሬ”፡-

አንዳንድ ሐሜት ጣፋጭና ፈታኝ ሊሆን እንደሚችል አትርሳ። አንዳንድ ወሬ ስሜትን በቅርብ የሚነካ ሆኖ ሲቀርብ ተታሎ ያልተረጋገጠ ወሬ ውስጥ መግባት ስለሚቻል ተጠንቀቅ። ወሬው ዕውነት ቢሆንም እንኳን በሚታሙ ሰዎች ላይ መረባረብ የእግዚአብሔር ሰው ባሕሪይ ካለመሆኑም ሌላ፡- ጌታ የሚፈልገው በደለኛው ተጸጽቶ ከጥፋቱ እንዲመለስ፥ንስሐም እንዲገባ እንጂ በሐሜት አበሳውን እንድንጠቋቆም አለ መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

### የሐሜት ክፋቱ ለባለቤቱ ፡-

ወዳጅን፥የሚኖሩበትን ሐገር፥መሥሪያ ቤትንና ቤተክርስቲያንን ወዘተ ማማት ሆነ መንቀፍ ከቆሸሸ ልብ የሚመነጭና ቅዱሳንን የሚበክል መርዝ ነው። ተቺዎችና ሐሜተኞች በሐገር ለሹመት፥ በመሥሪያ ቤት ለዕድገት አይመረጡም። ቢመረጡም እንኳ አይፀናላቸውም።

አንተ ግን የእግዚአብሔር ወዳጅ፥ነቃፊነትና ሐሜት መንፈሳዊ ቅሌት መሆኑን አስተውለህ፥በየዕለቱ መንፈሳዊ ዕድገትህ ራስህን ከዚህ ጠብቅ።

### ስለ ሰው መልካም መናገር፡-

“ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከቶ ከአፋችሁ አይውጣ።” (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4÷29)

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሰዎችን ለበጎ ነገር ማደፋፈር፥ማጽናናት ለፍቅርና ለፈርሐ እግዚአብሔር ማበረታታት እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችን እንዳይወጣ ታዘናል። ስለዚህ በአጠገባችን ሰው እየታማ ስንሰማ፥ለሚታማው ሰው ተስፋ ያለበትን፥ምሕረትና መታነጽ ያለበትን ነገር በመናገር፡- ሐሜተኛውንም ስለ ነገሩ እንዲፀልይ ማደፋፈር የሁሉም ክርስቲያን ግዴታ ነው።

### ቅዱስ ድፍረት፡-

ሐሜትን ለመቃወም ድፈር። በሐሜተኞች ፊት በመለሳለስ ከእነርሱ ጋር መተባበር እነርሱን በመቃወም ከሚመጣው መጠላት እጅግ የከፋ መሆኑን አስተውል። እነርሱን መቃወም ለጊዜው ያስቀይማቸው ይሆናል። ለዘለቄታው ግን የማይጠፋ ትምሕርት ይተርፋቸዋል።

ውድ ቅዱሳን፡- በከበረው የጌታ ደም ተዋጅተን የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች የሆንነው፥በዕምነት በሚሠራው በጸጋው መሆኑ ዕሙን ነው። ሆኖም “እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና፡ እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።” ተብሎ በዘሌዋውያን 19÷2 እንደ ተጻፈው፥ ከሐሜትና ከትችት ራሳችንን በማንጻት ይበልጥ መቀደስ ይጠበቅብናል። ተቀድሼ አብቅቼአለሁ ለማለት ስለማይቻል፥በዚህ መልዕክት የሚቀሰቀስ እንደማይታጣ እናምናለን።

(Take control Over Gossip and Criticism) ከተባለ መልዕክት ተተርጉሞ መጀመሪያ በጥቅምት ወር 1994 ዓም ያሰራጨነው።

## ትንሽ ሥራ ትንሽ ሥፍራ

የሰው ልጅ የነፍሱ ጥማት የመከናወን ስሜት ለማግኘት እንጂ ሐብት ለማካበት አይደለም። የሰውን ልጅ ለዘመናት ሲያንከራትት የኖረው ግን የሐብት ብዛት የመከናወንን ስሜት ያመጣል የሚል የተሳሳተ ግምት ነው።

በእግዚአብሔር አስተሳሰብ ትንሽ ሰው እንደሌለ ሁሉ፥ ትንሽ ሥፍራም ትንሽ ሥራም የለም። እርሱን የማይታዘዝ ሰው ግን ከእግዚአብሔር ክብር ራሱን ስለሚያጎድል የተዋረደ ወይም ከታሰበለት ያነሰ ነው።

በዮሐንስ ወንጌል 15፥1-11 ትዕዛዛቱን ብንጠብቅ በእርሱ እንደምንኖርና ብዙ ፍሬ እንደምናፈራ እናነባለን። የሰው ልጅ ሁሉ ዕውነተኛ መከናወን የሚያገኘው የተፈጠረበትን ዓላማ በመፈጸም ላይ ሲገኝ ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር አምላኩን ማክበር ነው።"ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል።"ይላልና። (ዮሐ 15፥8)

ዛሬ በዓለም ላይ በማንኛውም የኑሮ ዘርፍ ያሉ ሠራተኞች በብዙ ተስፋ መቁረጥና መነካከስ የሚታወቁት ከሐብት ማነስ ወይም ለሰው የሚያስፈልገው አንሶ ሳይሆን፥ ሰዉ የተሰማራው በራሱ ፈቃድ በመረጠው ሥራና አገልግሎት ላይ በመሆኑ ነው። ያለእግዚአብሔርም ፈቃድ በሥጋዊ ምኞቱ በመሰማራት፥ የሚያገኘው ፍሬ ለዓይኑ አምሮት እንጂ ለነፍሱ እርካታ ሊሰጥ ስለማይችል ነው፤ ስለዚህ ነጋዴው ነግዶ፥ ገበሬው አርሶ ዳኛው ፈርዶ፥ቄሱም ከሰበከ በኋላ ሲመሽ በመኝታው ውስጥ መጽናናት የማይመጣለት ከሆነ፥ ራሱን ከእግዚአብሔር ፈቃድ አንጻር መመርመር ያስፈልገዋል

እግዚአብሔር ወደ አናጺነት ሙያ ወይም ሐኪምነት፥ ወደ ፋብሪካ ሥራ ወይም ጥብቅና፥ ወደ ነጋዴነት ወይም ወንጌላዊነት ሊመራን ይችላል። ወሳኙ ነገር ግን ፥ እርሱ መምራቱና በፈቃዱ ውስጥ መሆናችን ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ትንሽነት ስለሌለው እንደ ፈቃዱ ያለንበት ሥፍራና ሥራ ሁሉ ክቡር መሆኑን መረዳት ይጠቅማል።በእርሱም መንፈስ የሚመሩት፥ያሉበት ጊዜና ቦታ ሁሉ ትክክል ነው። እነርሱም የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ። በሰው ዓይን ትንሽ የሚመስል በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እጅግ የከበረ ሥራና ሥፍራ አለ። በዚያም መከራ ቢኖርም ባይኖርም ብዙ ፍሬና ሰላም አለ። እግዚአብሔርም ይከብራል። ክብሩም ሕይወትን በማበልጸግ የነፍስ እርካታን ይሰጣል። የረካች ነፍስ ደግሞ በእስር ቤት ውስጥ እንኳ መዘመር ትችላለች፥እግዚአብሔር ይመስገን።

በዮሐ/ወ 15፥5 "... በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል" እንደሚል፡-እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተሰማራንበት ትንሽ መሳይ ሥራ ፍሬው መብዛቱ ብቻ ሳይሆን እርካታንም የሚያስከትል ነው። ምክንያቱም አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ የሚታዘዙትን መጎብኘት ስለሚወድና በጉብኝቱም የነፍስ ሐሴት ስለሚገኝ ነው። በሥጋዊ አመለካከት ትንሽ የሚመስልም ሥፍራ ታላቅ ልምምድ የሚቀሰምበት ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኛ ሥፍራ ሊሆን ይችላል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የመሆንን ጥቅም በአግባቡ የተረዳው ንጉሡ ዳዊት ለዚህ ነው፥ "አንተን ታምኛለሁና በማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ ፤ አቤቱ ነፍሴን ወደ አንተ አንስቻለሁና የምሄድበትን መንገድ አስታውቀኝ። ...አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ፤ ቅዱስ መንፈስህም በጽድቅ ምድር ይምራኝ።" በማለት የፀለየው።
(መዝሙር 143፥8-10)

*አንተስ የእግዚአብሔር ሰው? ባለህበት አገልግሎት ላይ ያስቀመጠህ እግዚአብሔር ነው? ውስጣዊ ሰላም አለህ? መልስህ አዎን ከሆነ ያለህበት፥ትንሽ ሥፍራም፥ትንሽ ሥራም አይደለምና አይዞህ ጽና፤ በትጋት ሥራ። የሕይወትህን ፍሬ ጻድቁ እግዚአብሔር በጊዜው ይገልጸዋል። ክብር ለተመሰገነው ስሙ ይሁን።*

***************

# የዘላለም ሕይወት

በመጽሐፍ ቅዱሳችን መሠረት ፦ ከአዳም ጀምሮ፥ ሰው ሁሉ በደለኛ ስለሆነ፥ የዘላለም ሕይወት የማይገባው መሆኑን እንረዳለን። እንዲህ ይላል፡-

"ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ አስተዋይ የለም፤እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ቸርነት የሚያደርግ የለም አንድ ስንኳ የለም። ጉሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው፤ በመላሳቸው ሸንግለዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤አፋቸው እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል ፤ እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፤ ጥፋትና ጉስቁልና በመንገዳቸው ይገኛል፥ የሰላምንም መንገድ አያውቁም። በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም።"
(ሮሜ 3 ፥ 11 - 12)

አዕምሮ ያለው ሁሉ ስለዘላለም ሕይወት በሚመለከት ጥያቄ ሊኖረው ስለሚገበው የሚከተሉትን ጥያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸውን አቅርበናል።



# ሰባት
# አበይት የሕይወት
# ጥያቄዎች
# ?

## 1. ኃጢአት ምንድን ነው?

ቅዱስና ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ያልተወደደውን በማድረግ በዓመፃ መኖር ኃጢአት ነው። "ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው..." (የዮሐንስ መ/5፥17)

## 2. ኃጢአተኛ ማን ነው?

ከአዳም የተወለደ ሁሉ ነው። "ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፡ሁሉ ተሳስተዋል:... ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤" (ወደ ሮሜ ሰዎች 3፥10ና 23)

## 3. የኃጢአት ዋጋ ምንድን ነው?

"... ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች።""የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና..." (ሕዝቅኤል 18፥4) (ሮሜ 6፥23)

## ሞትስ ምንድን ነው?

"... ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም፥ወደማይጠፋ እሳት..." መጣል ነው። (ማርቆስ 9፥44)

"ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው።በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።" (ራዕይ 20፥14-15)

## 4. እግዚአብሔር እንደሚወደኝ እንዴት አውቃለሁ?

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"
(የዮሐንስ ወንጌል 3፥16)

## 5. ይቅርታ እንዴት ይገኛል?

መድኃኒ ዓለም እየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን ብንከተለውና "... እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ... የልጁም የእየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል።"
(1 የዮሐንስ መልዕክት 1፥7)

## 6. የእግዚአብሔር ልጅ እሆን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?

"በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ እመን ..."
(የሐዋሪያት ሥራ 16፥31)
"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤"
(የዮሐንስ ወንጌል 1፥12)

## 7. የዘላለም ሕይወት እንዳለኝ እንዴት አውቃለሁ?

" ... ስለዚህም ሕይወት ፥ የማይዋሽ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ፥" "የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።"
(ቲቶ 1፥2) (1ዮሐንስ 5፥13)

"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን፡ የላክኸውንም እየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ፡ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።"
(የዮሐንስ ወንጌል 17፥3)

# በዕምነት፥የንስሐ ፀሎት

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ። ዓለም ተቀብሎ ይድንበት ዘንድ በሰጠኸው በልጅህ በእየሱስ አምናለሁ። ሞቶ በእኔ ፈንታ ፥ ትንሣኤውም ለእኔ መሆኑን አምኜ እቀበላለሁ።ጌታና አዳኜ ነው። አድነኝ፤ ልጅህ አድርገኝ። ስለ ስምህ፤ አሜን።

እየሱስ ጌታ ነው! ጌታ ይባርክህ።